Australian Government

COVID-19 VACCINATION

# አስትራዘነካ/AstraZeneca መረጃ

## አስትራዘነካ/AstraZeneca ክትባት

በአስትራዘነካ/AstraZeneca ክትባት እና በጣም ትንሽ የሆነ ችግር ሁኔታ መካከል ግንኙነት እንዳለ፣ ይህም የደም መርጋትና ትንሽ የደም ፕላተለት/platelet ደረጃ መቀነስ ይሆናል። ይህ ሁኔታ ትሮምቦሲስ/Thrombosis ከትሮስይቶፕኒ ስይንድሮም/thrombocytopenia syndrome (TTS) ህማም ምልክቶች ጋር ተብሎ ይጠራል።

ለኮቪድ/COVID-19 ክትባት ሁሉም ጐልማሶች እንዲወስዱት ይመከራል። እድሚያቸው ከ60 ዓመት በታች ለሆኑ የኮቪድ/COVID-19 መከላከያ ፕፊዘር/Pfizer ክትባትን እንዲወስዱ ይመረጣል። ይሁን እንጂ እድሚያቸው ከ60 ዓመት በታች ለሆኑ አሁንም ለአስትራዘነካ/AstraZeneca ክትባት መውሰድ በእነሱ ምርጫ ይሆናል። ውሳኔ ለማድረግ እንዲረዳዎ ሀኪምዎን ማነጋገር ነው።

የአስትራዘነካ/AstraZeneca ክትባት የሚሰጠው እድሚያቸው 60 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑት ሰዎች ነው።

### ሮምቦሲስ/Thrombosis ከትሮስይቶፕኒ ዝግመት ህማም/thrombocytopenia syndrome (TTS በሚል የሚጠራ) ምንድ ነው?

ትሮምቦሲስ/Thrombosis ማለት የደም መቆም ማለት ነው።

ትሮስይቶፕኒ ስይንድሮም/thrombocytopenia syndrome ማለት አነስተኛ የደም ፕላተለት ደረጃ መጠን ነው።

TTS በአስትራዘነካ/AstraZeneca ይሊከሰት የሚችል በጣም አነስተኛ የሆነ ችግር ነው። ይህ ከተፈጠረ በጣም ከባድ የሰውነት አካል ጉዳት ሊያመጣ ይችላል። TTS ለደም መርጋት ችግር ምክንያት ሊሆን ሲችል፣ ይህም በተለያየ የሰውንት አካል ላይ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ለደም ፕላተለት መጠን ማነስ ምክንያት ሊሆን ይችላል፣ ይህም ለደም መፍሰስ ችግር ሊያመጣ ይችላል።

### መቸ ነው የTTS የሚከሰተው?

ለTTS መፈጠር ጉዳይ ሪፖርት የተደረገው ይህን ክትባት መውሰድ ከተጀመረ በኋላ ከ 4 እስከ 42 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሆነ እና አብዛኛው የመጀመሪያ መጠን/dose አስትራዘነካ/AstraZeneca ክትባት ከተወሰደ በኋላ ነው።

### TTS ምን ያህል የተለመደ ነው?

TTS በጣም ያልተለመደ ነው። በአሁን ጊዜ ችግር ካለባቸው የተገመተው ለአስትራዘነካ ኮቪድ/AstraZeneca COVID-19 ክትባት ከወሰዱት ከ100,000 ሰዎች ውስጥ 1-2 ሰዎች የሚሆኑት ችግር እንደደረሰባቸው ነው። ነገር ግን እድሚያቸው ከ60 ዓመት በታች በሆኑት ላይ ከፍተኛ እንደሆነ፣ ይህም ከ100,000 ሰዎች ውስጥ በግንት 2-3 ሰዎች የሚሆኑት ሰዎች ችግር እንዳለ ነው። በእነዚህ ግምቶች ለበለጠ መረጃ በማግኘት ወቅታዊ ይሆናል።

### የሆኑ ቡድኖች በTTS ላይ ለበለጠ ችግር ያጋልጣሉን?

ምንም እንኳን TTS በአንዳንድ የእድሜ አንጋፋ ጎልማሳ ሰዎች ላይ ችግሩ እንዳለ ሪፖርት ቢደረግም፣ ነገር ግን በታዳጊ ጎልማሶች ላይ እንደሚታይ ነው። ለደም መርጋት አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል የሆነ ቅድመ ህክምና መድሃኒት እንደነበረ እናውቅም። ተመራማሪዎች ለዚህ እያጣሩ ነው።

## የTTS በሽታ ምልክቶች ምንድ ናቸው?

TTS ለሚከተሉት አንዳንድ የበሽታ ምልክቶች ሊፈጠር ይችል ይሆናል:

- ሃይለኛ ማለይቆም የራስ ምታት፤ ይህም:
  - ከክትባት መውሰድ በኋላ ቢያንስ ለ2 ቀናት ሊፈጠር ይችላል
  - በቀላሉ ብህመም ማስታገሻ መድሃኒት የማይሻሻል
  - በምትተኛበት ጊዜ ሊብስ ይችላል
- ማቅለሽለሽ ወይም ማስታወክ
- በግልጽ የማይታይ መደብዘዝ
- ለመናገር ችግር
- እንቅልፍ እንቅልፍ ማለት
- በድንገት አእምሮ መሳት
- የመተንፈስ ችግር
- የደረት ህመም
- የውስጥ እግር ማበጥ
- የማያቋርጥ የሆድ እቃ ህመም
- መርፌ ከወሰዱ በኋላ በቆዳ ውስጥ ትንሽ ደም መቁጠር።

እርስዎ ወይም ሌላ ሰው ለኮቪድ/ COVID-19 ክትባት ከወሰዱ በኋላ ከነዚህ ከባድ ችግሮች የሆነ ከተፈጠረ፤ በቀጥታ በስልክ 000 አድርጎ መደወል ይችላሉ።

## የአስትራዘነካ/ AstraZeneca ክትባቶች ጥቅም ከሚፈጥረው ችግር የበለጠ ነውን?

አዎ፤ ክትባት በመውሰድ የሚገኘው ጥቅም ከሚከሰተው ችግር የበለጠ እንደሆነ፤ በተለይ ደግም በእድሜ አንጋፋ ለሆኑ ሰዎች በኮቪድ/ COVID-19 የመያዝ ከተኛ ችግር ላለባቸው ነው።

## እድሜዎት ከ 60 ዓመት በታች ከሆነ እና ለመጀመሪያው መጠን/ dose የአስትራዘነካ/ AstraZeneca ክትባት ለመውሰድ ቀጥሮ ከያዙ ምን ማድረግ ይኖርብዎታል?

ለርስዎ የመጀመሪያ መጠን/ dose አስትራዘነካ/ AstraZeneca ክትባት ለመውሰድ ቀጠሮ ካስያዙ እና እድሜዎት ከ60 ዓመት ለሀኪምዎ ማነጋገር። ክትባቱን ለመውሰድ ወይም ላለመውሰድ ለመወሰን ሀኪምዎ ይረዱዎታል።

## ለርስዎ የመጀመሪያመጠን/ dose የአስትራዘነካ/ AstraZeneca ክትባት ከወሰዱ በኋላ የሁለተኛ መጠን/ dose ክትባት ጊዜ ከደረሰ ምን ማድረግ ይኖርብዎታል?

የTTS ስለመፈጠሩ ጉዳዮች በሙሉ ሪፖርት የተደረገው ለመጀመሪያው መጠን/ dose የአስትራዘነካ ኮቪድ/ AstraZeneca COVID-19 ክትባት ከተወሰደ በኋላ ነው። ለመጀመሪያው መጠን/ dose የአስትራዘነካ ኮቪድ/ AstraZeneca ክትባት ከተወሰደ በኋላ ከባድ ችግር ካልፈጠረብዎት፤ ታዲያ ምንም እንኳን እድሜዎት ከ60 ዓመት በታች ቢሆንም ለሁለተኛው መጠን/ dose ክትባት ለመውሰድ እምነት ሊያሳድርብዎት ይችላል።

## ቀደም ሲል የደም መርጋት ችግር ለነበረባቸው ሰዎች የአስትራዘነካ/ AstraZeneca ክትባት መውሰዱ ደህንነቱ የተጠበቅ ነውን?

ቀደም ሲል ሌላ ዓይነት የደም መርጋት ችግር ከነበረብዎት ወይም በደም መርጋት ችግር ጫፍ ላይ ቢኖሩም የአስትራዘነካ/ AstraZeneca ክትባት መውሰድ ግን ይችላሉ። የአስትራዘነካ/ AstraZeneca ክትባት በመውሰድ ቀጥሎ የ TTS ችግር በመፍጠር ላይ ቀደም ሲል የደም መርጋት የሚያሳይ ማስረጃ የለም።

## ለበለጠ መረጃ

ስለ አስትራዘነካ/ AstraZeneca ክትባት ጥያቄዎች ካለዎት፤ ሀኪምዎን ማነጋገር፤ በድረገጽ www.health.gov.au/covid19-vaccines-languages ላይ ገብቶ ማየት ወይም ለአገር አቀፍ ኮሮናቫይረስ እርዳታ መስመር በስልክ 1800 020 080 መደወል። ለትርጉማ አስተርጓሚ አገልግሎቶች በስልክ 131 450 አድርጎ መደወል።